## ውሸትን ማገለጥ 1

## ቶጲያ በውሸትና ቅጥፈት የተሞሏ

በኑረዲን አብደላ

ይህንን ቅጥፈት ደራሲው ሲጽፍ  ምንያህል የአንባቢን
ይታዘበኛል ወይንም ይህንን ፈትህ አል ሃበሽ መጻሃፍ አግኝተው የማንበብ እድል የላቸውምና የራሴ ውሸት ብጽፍም ማንም አያውቅም የሚል ግብዝ ጸሃፊ ነው

የቶጲያ  ውሸት ዘጋቢ የሚከተለውን  በአረብ ፈቂ መጻሃፍ  ያልተጻፈን ሰነድ ተጻፈ ብሎ የውሸት ዘገባ ያስነባል  ...ይህም የሚከተለው በቶጲያ የቀረበ  ነው

[በአረብ ፈቂህ ዘገባ መሰረት የስልጤ አዲያ ሱልጣኔት አዲ ገራድ ሙሪየስ የምትባል ሴት ልጁን ለኢማም አህመድ ገራድ ኢብራሂም አልጋዚ ዳረላቸው ]

ልብ በሉ ጸሃፊው በፍቱል አል ሐበሽ ገጹ አልጠቀሰም ፣
የቶጲያ ጸሃፊ ነጃሺ ከዲር ሻሞ ምኞቱ ኢማም አህመድ ስልጤ ሚስት ነበረችው ፣ ከኢማም ጋር ተገብተናል ነው ፣ ሰነዱ እውነት ቢሆን እሰየው ነበር ። ነገር ግን በፍቱል ሐበሽ ፈጽሞ ስለ ስልጤ ኢማሙ ያገባት የሚል የለም   የጸሃፊውን  ቅጥፈት ለማጋለጥ መረጃውን  የሚከተለውን በፍቱል አልሐበሽ ስለ ኢማም አህመድ ሚስቶችን ከነ ገጹ አቀርባለሁኝ ።

ቅጽ 1 ገጽ 47 አንዳንድ የሰራዊት አባላት ኢማሙን ሚስታቸው ድልወንበራ ወደ ከሃዲያን አገር አብራን ትሂድ ዘንድ አንፈቅድም ይህ ከርሶ በፊት የነበሩት አሚሮች ያልፈጸሙት ድርጊትና ተግባር ነው ብለው ተጠየቁ ኢማሙም ሚስታቸው የቀረበውን ክስ እንዲመለሱ ሰራዊቱ ፊት ተጠየቁ ሚስታቸውም ድልወንበራ አልመለስም አለች ፣

ኢማሙም ሚስታቸውን ይዘው ወደ ኢፋት ተንቀሳቀሱ

ቅጽ 1 ገጽ 57  በዚፋሕ  6 ቀናት ቆዩ የኢማሙ ባለቤት (ድልወንበራ) ዚፋህ ላይ ወንድ ልጅ ተገላገለች ስሙም መሐመድ ወጣለት ።

ቅጽ 1 ገጽ 106 ኢማሙና ባለቤቱ (ድል ወንበራ )

ወደፈለጉት አገር እንዲሄዱ .....

ቅጽ 1 ገጽ 114  የልብነድንግል የጦር አበጋዝ ተክለሃይማኖት ባሌ ሃገር  ላይ የነበረው በሙስሊም ሰራዊት በነ አቢበከር ቀጪን ተማረከ የተክለሃይማኖት ሚስት በቤቷ ተማረከች ፣ የተክለሐይማኖት ሚስት ኢማሙ ወርሰው አገቧት ፣እስልምናም ተቀበለች ልጅም ወለደች ኢማሙም ሐጀር የሚል ስም አወጡላት ።

ቅጽ 1 ገጽ 126  ባሌ ላይ የተክለሐይማኖት ሚስት የነበረችውን ሐጀር ስም ያወጡላት አስከትለው ጉዞ ጀመሩ ።

ቅጽ 2 ገጽ 35  የኢማሙ እቁባት ሐጅራ የአይብስ የቅርብ ዘመድ ናት የአባቱ ወንድም ልጅ ናት

ቅጽ 2 ገጽ 198 ሐራር ወንዝ ደረሱ የኢማሙ ሰራዊት የሐበሻውን ንጉሥ እህት ( የልብንድንግል እህት ሴት ልጅ) ማርከው ይዘው ወደ ኢማሙ ተመለሱ ፣ ኢማሙ ልጅቷን በጭን ገረድ ይዘዋት ልጅም ወለደች ።

ቅጽ 2 ገጽ 200 የኢማሙ ሰራዊት ትግራይ ገባ ሙስሊሞች ወደ እነርሱ መጥተው ማርያም ቤተክርስቲያን አጠገብ ሰፈሩ የኢማሙ ሚስት በዕቲያህ ቢንት መህፉዝ በዚሁ ቦታ ወንድ ልጅ ተገላገለች ስሙንም አህመድ አን ነጃሽ አሉት

ቅጽ 2 ገጽ 209 ኢማሙ ሱልጣን መከተር ወደ ሚኖርበት  መዝጅህ ደርሰው ከአንድ ማሳ አቅራቢያ ሰፈሩ ። የሱልጣን መከተርንም ልጅ አገቡ አስር ቀን ያህል ከተቀመጡ በኃላ እኔ ንጉሱን እከተለዋለሁ አልቀመጥም በማለት ተነሱ ።

አንባቢያን ከላይ የኢማሙ ሚስቶችና እቁባቶች የቀረበው በፈትህ አልሐበሽ በአረብ ፈቂ የቀረበ ዘገባ ይህ ሆኖ እያለ የቶጲያ ጸሃፊ ነጃሽ ከዲር ያልተጻፈ ውሸት መረጃ ለአንባቢ እውነት አስመስሎ ማቅረብ ትልቅ ወንጀል ነው ፣ ስለሆነም በቶጲያ መጸሃፍ በርካታ ሐሰት መረጃን አንድ ባንድ እያመጣን ለአንባቢ በማቅረብ እርምት እንሰጣለን







ይቀጥላል !

### ቶጲያ 1
### ስህተት አጋልጥ ቁጥር 2
### ኑረዲን አብደላ

ጦቢያ የሚባል መጸሃፍ የሃገራችን የመጀመሪያው ልበወለድ መጸሃፍ ሲሆን ደራሲው አፍወርቅ ገ/እየሱስ ናቸው ። ቶጲያ የሚባል መጽሃፍ የመጀመሪያ የሐገራችንን የእስልምና ታሪክ የሚቃረን የሚጋጭ በተቃርኖ የታጨቀ በደራሲ ነጃሺ ከዲር የቀረበ ነው ።

ጦቢያ ...ቶጲያ ልበወለድ በመሆናቸው ተመሳሰለብኝ

የቶጲያ መጽሐፍ በውስጡ በርካታ የሚጣረዝ በሐረሪና በሐረር ጥናት ያደረጉትን ጹሑፎች በመሰብሰብ በመገልበጥ የሐረሪና የሐረር ታሪክ ስያሜዎችን በመፋቅ በቦታው [ የስልጤ ቀደምት አባቶች ] በሚለውን ሐርግ በማስገባት የነባሩን የሐረሪን ማህበረሰብ ታሪክና ቅርሥ ሽሚያና ነጠቃ ከመጸሃፉ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ በዚህ አይነት ሽፍጥ ምንም ዓይነት በቋንቋ ፣ በጂግራፊ ፣ በስነልቦና ፣ በርኪኦሎጂ በትውፊትና በሰነድ ያልቀረበና በሌሎች ምሁራንና ተመራማሪዎች የቀረበውን ሰነዳዊ ዘገባዎችን የሐረሪ ፣ የሐዲያ ፣ የአርጎባ ፣ የሱማሌ የአፋር ወዘተ ታሪክ የባለታሪኩን ማህበረሰብ ስም በመፋቅ [የስልጤ ቀደምት አባቶች] በሚል በማስገባት እውነታ የሌለው ሃሰት ትርክት በመተረክ የሙስሊሙን ነባር ታሪክ በማጠልሸት አዲስ ፈጠራ አስመስሎ አቅርቧል ። ለዚህ የሚከተለው ስለ ሐረሪ በሐረሪ ታሪክ ተመራማሪ ጸሀፊ በዶ/ር አብዱማሊክ አቡበከር ለPHD ሟሟያ በቃረበው የሐረሪና እሴት እና ራሳቸውን የመሩበት ታሪካዊ ክስተቶች በሚለው ጹሁፍ ነባር ሐርላዊያን ማህበረሰብ እና ሐረሪዎች በእስልምና ስልጣኔና እድገት ያበረከቱትን አጠቃላይ ማህበራዊ እሴት እድገት የቶጵያ ጸሃፊ እንዴት አድርጎ የሐረሪን ታሪክን ጠምዝዞና አወላግዶ ወደ [ስልጤ ቀደምት አያቶች] እንደጻፈው የሚከተለውን በቶጲያ በገጽ 40 የሚከተለው ቀርባል

[ በዚህ የአብዱማሊክ አቡበከር መረጃ መሰረት የሀርላ መስራች በመባል በዋናነት የሚታወሱ ሶስት ቀደምት ጥንታዊዉ ሴማዊ ማህበረሶቦች መኖሪያ ተጠቅሰዋል እነርሱም
1- እሳንቃንጢጌ ( essankhanti Gey)
2- ጡቅንጌ (TukhunGey)
3- ኢታንቴጌ ( Etante Gey)
ጥንታዊ ሴማዊ ህዝቦች ይህንን ስፍራ ዋና ማዕከላቸው አድርገው ቢያንስ የሁለት ትውልድ እድሜ እንደኖሩ አብዱማሊክ አቡበከር መረጃ ይገልጻል ......በተከሰተው የወባ በሽታ ሴማዊ የሐርላ ማህበረሰቦች የኢሳንቃንጢጌ መኖሪያቸውን እየለቀቁ ወደ ሰሜን አቅጣጫ በመንቀሳቀስ ጡቅንጌ (Tukhun Gey) በሚባለው ስፍራ ሰፈሩ ። ጡቅንጌ በዳካርና ማዊር በሚባለው ለእርሻ ተስማሚ በሆነው ለም መሬት መካከል የሚገኝ ጠባብ ስፍራ ነበር ። .........በጡቅንጌ የ1ወይም የ2 ትውልድ ሰነበቱ .....ጡቅንጌ መሬት ስለጠበባቸው ተንስተው ኢታንቴ ( Etante Gey) በሚባለውሰፈሩ ፣ .....በዚህ ሁኔታ ከቀይ ባህር ጠረፍ እስከ መሐል ደቡብ ኢትዮጵያ ድረስ ይስፋፋሉ እነዚህ ጥንታዊ ማህበረሰቦች የስልጤ ቀደምት አባቶች ናቸው በተንቀሳቀሱበት በ3ቱ አካባቢዎች የኖሩ ማህበረሰቦች ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደነበሩ በአብዱማሊክ ጥናት ተገልጿል ፣ ቶጲያ ፣ ገጽ 39-40 ]
ከላይ የቀረበው ጸሃፊው ነጃሽ ከዲር የሐረሪ የዶ/ር አብዱማሊክ ስለ ሐረሪ እሴት ራሳቸውን የመሩበትና ያስተዳደሩበትን ታሪካዊ ጹሁፍ በስህተት አቅርቦታል ስህተቱም የሚከተሉት ናቸው
1- ጸሃፊው በሐረር ዙሪያ የሚገኙትን የሐርላ ጥንታዊው መንዶሮችን ስማቸውንም በትክክል አልጻፈም ፣
እሳንቃንጢጌ
ጡቅንጌ
ኢታንቴጌ
ዳካር
በሐረር ዙሪያ የምትኖሩ ዜጎች በዚህ በቶጵያ ጸሃፊ ከላይ በጸፈው ጹሁፍ የአካባቢው ስም ስቃቹህ መገረማችህ አልጠራጠርም ።
በእንግሊዘኛ የተጻፈው የዶ/ር አብዱማሊክ ጹሁፍ ትክክል ነው ። ነገር ግን አላዋቂ ሳሚ በንፍጥ ይለቀልቃል ሆነ ነገሩ ፣ በለማወቅ የሚጻፍ ትልቅ ውርደት ላይ ይጥላል ። ዶ/ር አብዱማሊክ ስለ ጥንት የሐረሪ መነሻ የሆነው የሐርላ ማህበረሰብ ቀደምት ሐረሪዎች ይኖሩበት የነበረው በሐረሪ ቋንቋ ስያሜውን ያገኘው ሰባቱ መንደሮች ውስጥ ከላይ የቀረቡት አላዋቂው የቶጲያ ጸሃፊ ለመጻፍ የተቸገረበትበ በሐረሪ ቋንቋ የተሰየሙትና ትርጉማቸውም የሚከተሉት ናቸው

እስኻንቲ ጌይ ( ከተማ ትሆን ነበር)
ትኹን ጌይ ( ከተማ ትሁን)
ኢታንቴ ጌይ ( ይህቺ ናት ከተማ )

የሐረሪ ነባር ህዝቦች እና የሐርላ ማህበረሰብ በሰባቱ ጥንታዊው የሐረሪ መነሻ መንደር ስያሜቸውን በሐረሪ ቋንቋ የተሰየሙ ናቸው ተብለው በታሪክ ሰነዶች በበርካታ ቦታ የሚጠቀሱት ሰባቱ መንደሮች በሐረር ዙሪያ የሚከተሉት ናቸው
1- ትኹን ጌይ
ከሐረር ጀጎል ደቡብ ምዕራብ በኩል ጂንኤላ አካባቢ
2- እስኻንቲ ጌይ
በጂጂጋ መንገድ ከጀጎል ክፍለ ከተማ 8 ኪ ሜ በረኸ ሰሪ አካባቢ
3- ሐሰን ጌይ
በአሁኑ ወቅት ሐመሬይሳ አካባቢ
4- ፈረቃ ጌይ
በጀጎል ክፍለ ከተማ በስተደቡብ ቡርቃ አብዱልቃዲር ጄይላን አካባቢ

5- ሐረዌ ጌይ
በአሁኑ ወቅት ሐረዌ ተብሎ በሚጠራበት አካባቢ
6- ሩቂያ ጌይ
ወደ ደደር መንገድ በሚውስደው አካባቢ የሚገኝ
7- ሳምቲ ጌይ
በጆጎል በስተ ሰሜን በአሁኑ ጃርሶ አቅጣጫ መንገድ
[የከተማ ባህል መፍለቂያ ሐረር ጆጎል ፣ መፍቱህ ዘከሪያ ፣ ገጽ 31 ]

ሌላው የቶጲያ ጸሐፊ በተደጋጋሚ ስህተቶችና ትልቅ ከታሪክ ጋር የሚጋጨውና የሚላተመው የሐርላ መስራች በሶስቱ መንደሮች ፣ ሶስቱ ሴማዊ ፣ የስልጤ ቅደምት አያቶች ናቸው ይላል ጹሁፉ ። ይህ በመሰረቱ መሰረትና መረጃ የሌለው አሉባልታ ነው ፣ የሐርላ ማህበረሰብ በሴማዊና በኩሻዊ ቋንቋ ባለቤት የተመሰረተ ስልጣኔ ነው ። የኩሽ ቀንቋ ተናጋሪ የሐርላ ነባር ማህበረሰብ በሐረርና በዙሪያው ታላላቅ ስልጣኔና አስተዎጸ ከደረጉት የአፋር ማህበረሰብ ፣ የሶማሌ ማህበረሰብ በታሪክ ጎላ ብለው ኩሻዊ ቋንቋ ቤተሰብ በሰነድ ብዙ የተሰነደላቸው ማህበረሰቦች ናቸው ፣ ከዚያ አኳያ በንጽጽር ቢቀርብ [የስልጤ ቀደምት አያቶች ] ተብሎ በድግግም በቶጲያ የቀረበው በታሪክ ሰነዶች እምብዛም ተጽፈው አይታዩም ።

ያም ሆኖ የስልጤ ማህበረሰብ ከሐዲያ ሱልጣኔት ፣ ከሌሎች ጋር በትብብር በርካታ አውንታዊ አስተዎጾ አበርክቷል ነገር ግን የአፋር እና የሱማሌ ኩሽ ተናጋሪ ማህበረሰብ ከዘቢድ እስከ ዘይላ ፣ ከኡጋዴን እስከ ህንድ ውቅኖስ በሐርላ የዋሻ ውስጥ ስእሎች ፣ መቃብሮች ፣ ዶሪዎች ማህበረሰብ ያበረከተው ትልቅ ጉልህ ሚና የነበርቸውና እስላማዊ መንግስት የመሰረቱ በርካታ በእስልምና ማስፋፋት ፣ በምጣኔ ሐብት ንግድ ወዘተ ታላቅ የኩሽ ቋንቋ ማህበረሰብ ባለቤት ናቸው ። ለታሪክ ሽሚያ ሲባል ሐርላ ስልጣኔ ሴማዊ ተናጋሪ ብቻ የስልጣኔ ውጤት ነው ማለት በነባሩ እስልምና ታሪክ መክድትና ማሾፍ ነው !!







ይቀጥላል !

**ቶጺያ ታሪክ ሳይሆን ምናብና ቅዠት**
**ውሸት አጋልጥ ቁጥር 3**
**በኑረዲን አብደላ**

በቶጺያ በተባለው መጸሃፍ የሚከተለውን ጽፏል
[የስልጤ ማህበረሰብ ሀረር ከተማ አካባቢን በመልቀቅ ወደ ጨርጨር ገመገም የተንቀሳቀሰበትን የአደሬ ማህበረሰብ ለብዙ ዘመናት ሳይረሳው ኖሯል ። ዛሬም በአደሬ ስነቃል ውስጥ ያንን የመለያየት ክፉ አጋጣሚ የሚያወሱ ስንኞች ትውፊቶች ስውር ተሰፍተው ይገኛሉ ለምሳሌ
ጌይ ወልዶው ጌይ ጊባእ
ጠይ ሰሪቤ ወራባ የግባእ
የአገር ልጅ ወደ አገርህ ግባ
በጥቁር ተራራ ጅብ ይግባበት
ቶጺያ ገጽ 290 ]

ጌይ ወልዶው ጌይ ጊባእ
ጠይ ሰሪቤ ወራባ የግባእ

ይህ መኽማኻ ሲናን ሐረሪዎች (ጌይ ኡሱእ ) የተናገሩት የተጠቀሙበት አንተ በምናብ እንደ ታየህ በቶጺያ እንዳሰፈርከው ቅጥፈት ሳይሆን ( ጌይ ኡሱአች ) ለእስልምና ዲን ማስተማር ፣ ለንግድ ፣ በትዳር በተለያዩ ማህበራዊ ትስስሮች ጌይ ኡሱአች ወደ ሌላ አካባቢዎች መስተጋብር በመፍጠር ከዋናው ሃገራቸው ( ጌይ ) በመራቅ ከዋናው ጌይ ውስጥ ያገኙት የነበረውና ጥብቅ ትስስር (Bond) ከነበራቸው ስልጣኔ (ኩሙል ሂርፊት) ውስጥ የእስልምና ትምህርት ፣ ቋንቋ ፣ ባህል አዳዕ ፣ ሓላ አመል ፣ የእደጥበብ ሙያ ፣ የተሟላ ባህላዊ እሴትና አፎቻ ወደ ተበጣጠሰ በሌላው አካባቢና (ሂርፊት ቁቡል) ከጌይ ስልጣኔ በመራቅ በሌላ ባህል ፣ እምነትና አኗኗር ዜይቤ ስር በመቅለጥ በመቅረት የሚፈጥረው Cultural Assimilation የሚፈጥረው ክፍተትና ጌይ ወልዲ ወይም ጌይ ኡሱነት ያጎልበታል ፣ ይኮስስበታል ይህ ያጎደለበትና የኮሰሰበትን ደግሞ ሐረሪዎች ጠይሰሪ በማለት ነው የገለጡት ። ጠይሰሪ (ድቅድቅጨለማ፣ ጨለማ ተራራ) ማለት ምልከታው እውቀት የሌለበት ፣ እስልምና ያልዳበረበት ፣ መሃይምነት የተስፋፋበት ፣ የሚወለደው አዲስ ትውልድ ለአደጋ ይጋለጣል ፣ እስልምና ፣ የዲን እውቀት ፣ ትምህርት ፣ ባህል ፣ ፍቅር ካልዳበረ ፣ የሰው ልጅ አስተሳሰብ ወደ አውሬነት ተቀይሮ ጦርነት ይከሰታል ይህንን ነው ሐረሪዎች አውሬነት ( ወራባ ) ለዚህ ሁሉ መነሻ የሆነው (እስልምና እውቀት ያልዳበረበት ፣ በጠይሰሪ) ምልክት አድርጎ በሐረሪ መኽማኻ ስንኝ የቋጠረው ።

እነዚህ ሁሉ ዝርዝር ተደርገው የቀረቡት በሐረሪ ታሪክ የቋንቋ ጥናት በሁለት ታሪክ ሰነዶች ተጠቅሰዋል እነርሱም በመስኖይ በጃሊዩይ ዝርዝር ዝገባ ላይ ነው የቀረቡት ።
ሐረሪዎች ( ጌይ ኡሱአች ) እንደዛሬው የየብስና የየባህር ጉዞ ትራንስፖርት ባልተስፋፋበት ዘመን ተራራና ሸንተር አቋርጠው የተጋዙበትና ከሌላው ማህበረሰብ መስተጋብር ሲፈጥሩ በዚህ መስተጋብር ተግዳሮቶች ሲከሰት ለዚህ ተግዳሮቶች የአካቢውና የመንዶሮቹ ስም በመጥቀስ የገለጹትም በላይ የቀረቡ በመስኖይና በጃሊዩይ ባህረ መዝገብ ሰነዶች ነው ። የጃሊዩይ የመስኖይ ስነቋንቋ ፣ ባህል ፣ ታሪክ ፣ የኑሮ ዘይቤ ፣ ሐረሪዎች( ጌይ እሱአች) ምን አይነት ስልጣኔ እንደነበራች ፣ በጠቃላይ በውስጡ በያዛቸው ዝርዝር ጹሁፍ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በርከታ ሙሁራን ጹሁፍ ጽፈወል ከነዚህ አውሻሚ ፣ ከቢር አብዱልሙይሄይሚን ፣ መሐመድ ኢብራሂም ሱሌይማን እንዲሁም Wolf leslaw , chansons Harar የሚጠቀሱት ናቸው ።

ከላይ በዝርዝር ለማመልከት እንደመሞከርኩ በመስኖይ ሰነድ ላይ ሐረሪዎ ለእስልምና ዲን ፣ ለንግድ እንዲሁም በጋብቻና ወዘተ መስታጋብር ያደረጉበትን እንደሚከተለው ቀርቧል

ቦረን ባድዋ ቢርዲዞም አዳዊና
ጌይ ባድዚና ናስተሺና ቢርዲ ዛሌልባና
አፍተል ባድዋ ሃፈንዞም አዳዊኒና
ጌይ ባድዚና ናስተሻና ሃፈን  ዘሌልባና
ሌለ ባድዋ ኡሱኽዞሞ አዳዊኒና
ጌይ ባድዚኛ ናስተሻና ኡሱኽ ዘሌልባና
ቃለ ባድዋ ኪንቼችዞሞ አዳዊኒና
ጌይ ባድዚኛ ናስተሻና ከንቼች ዘሌልባና
ዋሩፍ ባድዋ ሐንደቅዞማ አዳዊኒና
ጌይ ባድዚኛ ናስተሺና ሐንደቅ ዜሌልባና
ኢሳ ባድዋ ሲሰዞማ አዳዊኒና
ጌይ ባድዚኛ ናስተሺና ሲሳ ዘሌልባና
እያለ እያንዳንዱን ከተማ መንዶሮች ኢፋት ፣ ሱማል ፣ቦረና ኦሮሞ ፣  አፍተል ዘይላ ፣ ወዘተ   የመስተጋብሩንና ተግዳሮቶች እያመለከተ በንጽጽር ደግሞ ጌይ ምን እንደምትመስል በመስኖይ ያመለክታል ነገር ግን በመስኖይ ስለስልጤ ምንም የተጠቀሰ ሰም የለም  [ ቀጠብቲ ሙዳይ : ገጽ 203 ]

በተመሳሳይ በጃሊዩይ ዘገባ በገጽ 213 ላይ እንደላይኛው  በጃሊዩይ ተራ ቁጥር 128
ጌይ ወልዶው ጌይ ጊባእ
ጠይ ሰሪቤ ወራባ የግባእ
ስንኝ ቀርቧል  የቀረበው ለሐረሪ ( ለጌይ እሱኡ/ ለጌይ ወልዲ ) ብሎ ለሚጠራው ነው ። ምሳሌ እርስ በእርሳቸው የማይተዋወቁ  ሁለት ሐረሪዎች ሲገናኙ እርስበእርሳቸው የሚተዋወቁት እንዲህ በማለት ነው  [ጌይ ወልዲንተኽ? ጌይ ቀኸት ተሽ  ? በማለትነው ]
እዚህ ባለንበት ውጭ ሃገር  አንድ የሐረሪ ብሄረሰቡ በአጋጣሚ ቢሞት እርስ በእርሳችን በስልክ ወይም በአካል ተገናኝተን የምናውራው  [አሃድ ጌይ ወልዲ ሞታ]  በማለት ነው ። ነገር ግን ለሌላ ኮሚኒቲ ስንግልጽ (ስናስረዳ አንድ ሐረሪ ሞተ በማለት ነው)
ስለሆነም የቶዲያ ጸሃፊ ነጃሺ ከድር
ጌይ ወልዶው ጌይ ጊባእ
ጠይ ሰሪቤ ወረባ የግባእ

ብለው ሐረሪዎች የተናገሩት ለስልጤ ማህበረሰብ ነው ያለው ፣ ፉጹም ስህተት ነው ። ሐረሪዎች ጌይ ኡሱእ ፣ ጌይ ወልዶው ብለው የሚጠሩት የራሳቸውን ብሄር እንጂ ሌላ ብሄረሰብን አይደለም ። (ጌይ ኡሱአች) ሐረሪዎች ጌይን ለቀው ለሃይማኖት አስተምሮ ፣ ለንግድ ፣ በመንደር ገዢነት ፣ በጦር አበጋዝነት ፣ በልዩ ልዩ ምክንያቶች በሄዱበት አካባቢ ከዋናው መነሻ ሃገራቸው ጌይ (የእውቀት መዕከል መነሻቸው) በመራቃቸው የቀረበ ጥሪ ነው ፣ የዚህ ስንኝ ጥያቄ ዛሬም በዲያስፖራው ለሚገኙ ሐረሪዎች ጌይ ወልዶው ጌይ ጊባእ እየተባለም ይቀርባል ። በሌላ በኩል ከሐረር (ጌይ ኡሱአች) ወደ አዲስ አበባ ፣ ድሬደዋ ፣ ደደር፣ ጉርሱም አሁን ደግሞ በውጭ አለም ተጉዘው በሰፈሩበት ሃገር የእስልምና ት/ቤቶች (መድረሳ) ፣ መስጂዶች ፣ አፎቻ ፣ ባህል ፣ ቋንቋ ወዘተ በማቋቋም ቀጣይ ትውልድ በጥሩ በሐረሪ እሴት ያዳባሩ ሐረሪዎች( ጌይ ኡሱአች) እነርሱ [ጠይሰሪ] ውስጥ አይደለም ነገር ግን ዛሬም ጌይ ኡሱእ ሆኖ ሐይማኖቱ ፣ ባህሉን ቋንቋ ፣ ወግና ልምዱን በአጠቃላይ የሐረሪን እሴት የዘነጋ ይህ በጠይ ሰሪ ውስጥ ነው መልሱም ጠይ ሰሪቤ ወረባ የግባእ ተብሎ የሚመከረው ።

### ቶጂያ ሃላፊነት የጎደለው








### ሐሰተኛ መረጃ
### ስልጤ ህዝብ ታሪክ ጋር የሚጋጭ
### ቁጥር 4 ውሸት አጋልጥ

[ ከሼኽ አባዲር በፊት ሀረር የምትባል ከተማም ሆነ ሀረር የሚባል ግዛት አልነበረም ። አደሬ የሚባል የተለየ ጎሳም አልነበረም ። ሼይኽ አባዲር በቆረቆሯት አዲሳ ሀረር ከተማ የመኖር ዕድል ያገኘው የሀርላ ማህበረሰብ ክፍል ራሱን አደሬ ብሎ ይጠራ ጀመር ሌሎች አደሬ ብለው ይጠሩት ጀመሩ ። ሼይኽ አባድር ከሀርላ ማህበረሰብ ጋር በፈጠሩት መስተጋብር መሃል "አድሬ" የሚባል ማንነትና " ሀረር " የምትባል ከተማ ተከሰቱ ። ቶጂያ ፣ ነጃሺ ከዲር ሻሞ ፣ ገጽ 286-287 ]

ከላይ በቀረበው ዘገባ ነጃሺ መግለጽ ማስመር የፈለገው ለ ሐረሪ ማህበረሰብ ላለው ጥላቻ በግልጽ አመልካችና ሃላፊነት የማይሰማው ግለሰብ መሆኑ በተደጋጋሚ የጹሁፉ አጻጻፍ የብሄረሰቡን ማንነት መጠሪያና ሐረሪ መሆኑ እያወቀ በእብሪት ሃላፊነት በጎደለው ለማሸማቀቅ አደሬ እያለ በብዙ ቦታ በመጽሃፉ ላይ ሰፍሯል ይህ የግለሰቡ አላዋቂነት አመልካች ነው ። በነገራችን አደሬ የሚለው ግዕዝ ቃል አደረ ፣ የቀየ ፣ የተደላደለ ፣ የረጋ የመሬቱ ባለቤት አመልካች ቃል ነው ነገር ግን የሐረሪ ማህበረሰብ የማነቱ መገለጫ ስያሜ ራሱን የገለጸበት ሐረሪ በሚለው ከሐርላ አብራክ የወጣና ዛሬ ላይ ሐረር ከተማ ላይ እስላማዊ ስልጣኔውን ገንብቶ ለአለም ያስተዋወቀበት [ አን ሐረሪ ባዴም ሐረር ] ብለው ማነታቸውን የገለጹበት ነው ።

ሁለተኛ ነጥብ አባዲር ከመጡ በሃላ ነው አደሬ የመጣው ከዛ በፊት አደሬ የሚባል ጎሳ የለም ለሚለው
መልሱ የሚከተለው ነው ።
ሼኽ አባዲር ከመምጣታቸው በፊት የዛሬው ሐረሪ ማህበረሰብ ትናንት በሐርላ ሰባቱ ጌይ
በ7 ጌይ መንደሮች እስኻንቲ ጌይ ፣ ቱኹን ጌይ ፣ ሐረዌ ጌይ ፣ ሩቂያ ጌይ ፣ ሐሰን ጌይ ፣ ፈረቃ ጌይ ፣ ሳምቲ ጌይ ይኖሩ
ነበር በዚህ ወቅት ነባሩ ማህበረሰብ ራሱን ጌይ ኡሱ (መንደሩ ነዋሪዎች) ብለው ራሳቸውን መጥራት የጀመሩት
[History Of Harar and Hararis , p 30]
በሰባቱ ሐርላ መንዶሮች በስፈረሩበት ወቅት ራሳቸውን የሚጠሩት ጌይ ኡሱ ( ከላይ በዝርዝር በቀረቡት ጌይ ውስጥ
ነዋሪዎች ) በማለት ነበር መገለጫቸው የሚገልጹት ። ይህንን ጥንታዊው የሐርላ መገለጫ ጌይ ኡሱ ዛሬም ድረስ
ሐረሪዎች እርስ በእርስ ሲተዋወቁ
ጌይ ወልዲንተኽ ? ጌይ ቀሃትንተሽ ? በማለት ይጠያየቃሉ ።
ሦስተኛ መልስ ሼኽ አባድር ከአረብ አገር የመጡ የሃይማኖት አባት ናቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አረበኛ ነው
። ነገር ግን ነባሩ [ጌይ እሱ] የሚናገረው [ጌይ ሲናን ] ቋንቋ በሰባቱ የሐርላ ጥንታዊዉ መንደር ውስጥ ይጠቀሙበት
የነበረው ቋንቋ ጌይ ሲናን ነበር ዛሬም [ጌይ ሲናን ነሳናና]
አራተኛ መልስ አሚሮቻች የሚጀምረው ጌይ አሚራች
የመጀመሪያው ከሼኽ አባድር በፊት በሳምቲ ጌይ ላይ ነበር አሚር ሐቦባ ቢን ሃሩን ቢን ኢስሃቅ ቢንዓሊ ቢን
እዘዲን በአሚሪነት መጀመሪያ የተሾሙት ።
[ ጀድወል አሻሽ ወሻሚ በእጅ የተጻፈ የአረበኛ ሰነድ]
በታሪክ ምሁር አው ሻሚ የቀረበ ነው።

ይህንን በተመለከ የታሪክ ምሁራን ከአባድር በፊት በሐርላ ምድር ሐረሪዎች ነባር ህዝቦች ለመሆናችን
የዩሪች ብርካምፐወር ዘገባ
የሐረሪ ( አደሬ) ጎሳ አባዲር ከመምጣታቸው በፊት የሐርላ ማህበረሰብ እንደነበር በሚከተለው መረጃ የሚከተለው
ያስነብባል ።
The islamization and the Muslim Shrines of Harar plateu
Ethnic dynamic and changes -
By Ulrich Braukamper

Who were Harala and what can be said about their ethnic origin? There are three idenifiable populations who have dominated the history of the Harar plateau during the last four centuries: the Harari (Adare), Somali and Oromo. The question arises to what extent the Harala can be linked with one of them.

The present inhabitants of the Harar plateau ascribe all archaeological sites and ruins of stone-built necropolis, store-pits, houses and mosques of that to the Harala. From the contemporary peoples of the area of our concern only the Harari were culturally close to the Harala as the representatives of a highly developed peasantry with centres. Moreover, there are some striking similarities in the technological standards and even in a structural details between the ruined "Harala" sites and the architecture of Harar town. For instance, the Harari store-pits, as described by Yusuf Ahmed (1960, pp. 29 sqa.) resemble in their form and mode of construction the so-

called bolla Harala, which are frequent in Chercher and still used by the present-day Oromo.
ሌለኛው የታሪክ ምሁር

ፕ/ር ላጲሶ
የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መሠሪያዎች
ገጽ 77
በዚህ አኳያ በአካባቢው ከተጠቀሱ ሱልጣኔቶች በተለይም ከ896 እስከ 1577 ድረስ በሰባት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የሸዋ ፣ የይፋት ፣ የአዳልና የሐረር ህዝቦች ሥርዎ መንግስታትና ሱልጣኔቶች በተለይም በኤደን ባህረሰላጤ በአዋሽ ጨርጨር መካከል በአንድ በተወሰነ የመሬት ክልል በጊዜ ፣ በሥርዓት ፣በኢኮኖሚ ፣ በሃይማኖት በባህል እርስበእርሳቸው እንዴት በቅርብ እንደተያያዙና እንደተወራረሱ በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ታይቷል ። በተጨማሪም በዚህ ጥናት በሐረር ታሪካዊ ግምብ ውስጥ የአደሬ ሴማዊ የቋንቋ ማህበረሰብ በሥፍራና በጊዜ በሃይማኖትና በባህል የጥንት ሸዋ ፣ ይፋት አዳልና ሐረር ሱልጣኔቶች ተከታይና ወራሽ እንደሆነ ከሰነዱ መረጃ ታውቋል ።

የስልጤ ምስክር ከስፈለገ መረጃ
ከይረዲን ተዘራ [ሴረ ገጽ 26]
[ሴረ የስልጤ ህዝብ ታሪክ ፣ በከይረዲን ተዘራ ፣ ገጽ 26]
ስለ ሐረሪ ሐርላ ማህበረሰብና ከአባዲር በፊት በመሬቱ ነባር መሆኑ
አያሌ ጎሳዎችና ማህበረሰቦች የተከፈለ በእንስሳት እርባታ በእርሻና በንግድ ተግባራት የተሰማራ ብሎም በመንግስታዊ ስርዓት የሚኖር አንድ ሐርላ የተባለ አገርና ህዝብ እንደነበረር ከዘመኑ መረጃዎች በትክክል ለማወቅ ይቻላል ። በመሆኑም በእነዚህ በተጠቀሱት የአርኪኦሎጂ ፣ የትውፊትና የታሪክ መረጃዎች መሠረት ከደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊዉ ህዝቦች አንዱ በዘር በቋንቋና በሃይማኖት በደቡብ ምስራቅ ከዛሬው የሐረሪ (አደሬ) ህዝብ ጋር የቀረበ ታሪካዊ አንድነት ያለው የሐርላ ህዝብ ነው ( የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሰረቶችና መሳሪያዎች ፣ ገጽ 97 ፣ ፕ/ር ላጲሶ ጌ ድሌቦ )
[ ሴረ የስልጤ ህዝብ ታሪክ፣ ከይረዲን ተዘራ ፣ ገጽ26 ]
ገጽ 24 ሴረ የስልጤ ህዝብ ታሪክ ከይረዲን ተዘራ
የሐርላ ህዝብ የሐረሪ ህዝብ አባት ናቸው ተብለው የሚታመኑት ሼኽ አባድር ወደ ስፍራው ከመምጣታቸው በፊት በስፍራው የነበረና ከሐረሪ ቋንቋ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሴማዊ ቋንቋ የሚናገር ሙስሊም ማህበረሰብ ነበር በማለት ኡርሊች ብራውካምፐር የRobbecchi Bricheti u189 : 479 Cerulli 1957-64:60 የሚባሉ ምሁራንን ጥናት መሰረት በማድረግ ይናገራሉ ።
ኡርሊች ብራውካምፐር እንዳስቀመጡት የሀርላ ህዝብ የሴማዊ ቋንቋ የሚናገርና ቋንቋውም ከሀረሪ ህዝቦች ጋር እንደሚመሳሰል ገልጸዋል ።
ገጽ 26 ሴረ የስልጤ ህዝብ ታሪክ
ይህ ህዝብ በአርኪኦሎጂ ፣ በታሪክና በትውፊት መረጃዎች መሰረት ከደቡብ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ህዝቦች አንዱ በዘር ፣ በቋንቋ በሃይማኖት በደቡብ ምስራቅ ከዛሬው ሐረሪ /አደሬ/ ህዝብ ጋር የቀረበ ታሪካዊ አንድነት ያለው የሀርላ ህዝብ ነው ።
ገጽ 141 ሴረ የስልጤ ታሪክ ከይረዲን ተዘራ
የሐረሪ -ስልጤ ህዝቦች ታሪክ የእስልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ቀዳሚ ታሪክ መሰረት ያደረገ ነው ። በ7ኛው ክፍለዘመን ከታላቁ የእስልምና ሀይማኖት መሪ ነብዩ መሐመድ ( የአላህ ሰላምና ሰላት በእሳቸው ላይ ይሁን) መነሳት ጋር በመካከለኛው ምስራቅ በደቡብ አውሮፖ በሰሜን አፍሪካ እስልምና ሐይማኖት በከፍተኛ መስፋፋቱን የታሪክ ሰነዶች ያስገነዝባሉ ። ታሪካቸውም [የስልጤና የሐረሪ] የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ባህላዊ ገጽታን የሚያንጸባርቅ ነው ። ከ8ተኛው ምዕተ ዓመት (ጀምሮ) በአንድነትና በወንድማማችነት ሆነው በቀይ ባህር ፣ በዳህላክ ደሴቶች ብሎም በጠረፍ ወደቦች የንግድ ስራዎችን ለዓለም አስተምረዋል በማለት (የአብዱልፈታህ) ጥናት አትቶ የሁለቱ ህዝቦች ታሪካዊ አንድነት ከ7ኛው ክፍለ ዘመን የእስልምና ሐይማኖት መነሳት ጋር .......

የሐረሪ ማህበረሰብና የእስልምና የተቀበለበት
ቅድመ አባዲር ከመምጣታቸው በፊት
ታላቁ የሐረር ታሪክ ሙሁር ኡስታዝ ዩሱፍ አብዱረህማን ሼኽ አላህ ይርሃማቸውና በአረበኛ በጻፉት ርእሱ
[ ታሪኽ መመለከቱል ሐረር ኢስላሚያ ] ወይንም
በአማረኛው ሲተረጎም
እስላማዊ ግዛት የሆነችው የሐረር ከተማ ታሪክ አጭር ዳሰሳ ብለው በጻፉት ላይ የተወሰደ
እስልምና ወደ ሐረር አካባቢ የመጣው በሩቂያ ጌይ በተባለው አካባቢ ሲሆን ይህም በፈረንጆቹ 615 አካባቢ የገባው በሰይዲና ኡሱማን ኢብኑ አፋን እጅ ነበር ። ከሳቸው ጋር ሚስታቸው ሩቂያ ቢንት ረሱሉላህ የነቢያችን ሴት ልጅ የሆነችው አብረው ነበሩ እንደዛውም አብዱረህማን ኢብኑ አውፍ እና 14 ሙሃጂሮች (ስደተኞች ) አብራቸው ነበሩ ። ይሄም የሆነው በ615 እኤአ በመጀመሪያ ሂጅሪያቸው ላይ ነበር ። ረሱል መሐመድ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ወደ መዲና ሒጂራ ከማድረጋቸው ስምንት አመት በፊት ነበር ። እነኚህ ወደ ዘይላ ሐረር አካባቢ (ሐርላ ሩቂያ ጌይ) ሂጅራ ያደረጉ ሰሃባዎች ( ስደተኞች) አራት ወራትን ረጀብ ፣ ሻአባን ፣ ረመዳን እና ሹዋል ቆይተው ወደ መካ ሃገራቸው ተመለሱ ።

ማጠቃለያ የሐርላ ነባር ጌይ ኡሱአች በሰባቱ መንደር በሃላ አው አባዲር በቆረቆራት ሐረር ጌይ ስር ተሰባሰቡ አዲስ የተጠናከረ ተቋምና የእስላም ባህል ግንባታ ተጀመረ በአብጀድና በሐርላ አዲስ ስያሜ ሐገራቸው ላይ አውዚና አባዲር ባድዚና ሐረር አንሐረሪ እያሉ ታላላቅ የእስልምና ሊቃውንት
ሼኽ ሐሺም አልሐረሪ
ሼኽ አቡ ሸዋሪብ አልሐረሪ
ሼኽ አቢ ዘሪ አልሐረሪ
ሼኽ አብዱላሂ አልሐረሪ
እያሉ በሐረሪ ማንምነት ይገለጻሉ

## ቶጲያ
## ቁጥር 5 ውሸት አጋልጥ
## ኑረዲን አብደላ

በቶጲያ በገጽ 101
የስልጤ ጎጆ ቤት ባህላዊ ቤት በስእል ምስል በቶጲያ መጽሃፍ በገጽ 101 ቀርባል ( ምስሉን እንድታዩት ለጥፍኩት) ደራሲው ይህንን ምስል በመለጠፉ ምስጋናዬ የላቀ ነው ፣ ደራሲው ነጃሺ ከዲር የስልጤ ቀደምት አባቶች የሐርላ መንግስትና ስልጣኔ መስራችና የስነጥበብ አዋቂዎች በማድረግ በበርካታ ቦታ በድድግሞሽ መረጃ የሌለው በቶጲያ ተስተውላል ፣ ነገር ግን በገጽ 101 ያቀረበው ጎጆ ቤት ሥእል ጸሃፊ ከሚጽፈው ጋር የሚጋጭ ነው ። ምክንያቱም ሐርላ ማህበረሰብ ገናና እና ከሚታወቁበት አንዱ በእደጥበብ ስራ ነው ይህንን በተመለከተ የተከበሩ ፐ/ር ላጲሶ የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶች ገጽ 97 የሚከተለው ቀርቧል ።
[ ከዛሬ አራትና አምስት ሺህ ዓመታት በፊት ገደማ ጀምሮ በእንስሳት እርባታ በእርሻ በእደጥበብ ተግባራት የተሰማሩና በአዋማዊ ሃይማኖቶች የተደራጁ ብዙ ጥንታዊ የሐርላና የሐዲያ ተዛማጅና አጎራባች ህዝቦች ይኖርባቸው እንደነበር በግልጽ ያሳያሉ ።]
ይህ እደጥበብ የቤቶችና መስጂዶች ፣ የውሃ ጉድጋዶች
ግንባታዎች በሐርላ መንደሮች በድንጋይ ጥበብ የተሰራ ቤታቸው በተለያዩ ቦታዎች ዛሬም ድረስ ይገኛል ከነዚህ ለአብነት በአርጎባ መንደር አርጎባ ፣ የሐረር ባህላዊ ቤት ጀገል ቤቶች፣ በግንብና በድንጋይ የተገነቡ እድሜ ጠገብና

መስጂዶች በጦርነት ሳይወድሙ ህያው ሆነው የሚገኙ ናቸው ፣ እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ለቶጲያ ጸሃፍ ነጃሺ ከዲር የማነሳው የስልጤ ቀደምት አባቶች በሐርላ ስልጣኔ ግምባር ቀደምት ሚና ነበራቸው እያለ በመጽፉ ድፍን የጻፈው ታዲያ እንዴት የሐርላ ማህበረሰብ በድንጋይ ቤቶችና በእድጥበብ ስራ የተካኑ የስልጤ ቀደምት አያቶች ለምን የግንብ ቤት ወይም ለምን በድንጋይ የተገነቡ ቤቶችን አልገነቡም ? የስልጤ ቀደምት አባቶች በቶጲያ ገጽ 101 ከሐርላ ከድንጋቤት ጥበብ ወደ ስልጤዞን ሳር ቤት ጎጆ ግንባታ የሚያመለክተው በዚህ መረጃ መሰረት የስልጤ ቀደምት አባቶች በሐርላ የእደጥበብ የግንብ ሥራ ግንባታዎች ላይ ተሳትፎ እንዳልነበራቸው በቶጲያ በገጽ 101 ያቀረብከው ስእል አመልካች መረጃ ነው ። ከላይ የቀረበ መረጃው የሚያመለክተው የቶጲያ ጸሃፊ እንዳለው በሐርላ ስልጣኔውን የስልጤ ቀደምት አባቶች ግንባር ቀደም ሚና የነበራቸው ሳይሆን የሐርላ ስልጣኔው ተካፋይ እንኳ በእደጥበብ ሚና እንዳልነበራቸው በግልጽ አመልካች ነው ፣ ይህ ባይሆን ኖሮ የስልጤ ቀደምት አባቶች አሁን በሰፈሩበት በሐርላ ስልጣኔ ባገኙት የእደጥበብና ቤት ግንባታ ልምድ እንደ ምስራቅ ሸዋ አካባቢ በኖራ መንደር ፣ በያስቢር ወዘት ፣ በአርጎባ መንደር እንደ ደዌይ ፣ ረሂመዶ ፣ ሾንኬ ፣ በሐረር አካባቢ የጆጎል የሐረሪ ግንብ ባህል ቤት ፣ በግንብ የተገነቡ መስጂዶች እንዲሁም በሐረር ኮሮሚ አርጎባ ፣ ኡመር ዲን ፣ ሳቆይ ወዘተ መንደር ግንብ ቤቶች የኪነጥበብ ህንጻ እንዳየነው ሁሉ አሁን ስልጤ በሰፈረበት በስልጢ ዞን ባህላዊ ጎጆ ቤት ሳይሆን በግንብ በድንጋይ የተገነቡ የጥበብ የስልጣኔ ስራና እድሜ ጠገብ ቅርስ እናይ ነበር ። በቶጲያ መጸሃፍ በተደጋጋሚ እጅግ ተጋንነው የስልጤ ቀደምት አያቶች የ ሃርላ ስልጣኔ ግንባር ቀደም ሚና እንደነበራቸው ደጋግመህ ብትጽፍም ነገር ግን ምንም አይነት ትላልቅ እስላማዊ አሻራ የመስጂዶችና የቤት የኪነጥበብ ቅርስ እንዳልገነቡ የገጽ 101 ያቀረብከው የስልጤ የሳርቤት ጎጆ የስልጤ ቅድመ አያቶች በሐርላ ማህበረሰብ ውስጥ በስልጣኔ በተለየም በቤት ግንባታ ጥበብ ሥራ ምንም የሚታይ ሥራ እንድልነበረበቸው የራስህ መረጃህ በገጽ 101 አመልካች ነው ። ይህንን በተመለከተ Braukamper.U የሚከተለወን ያስነብባል

The islamization and the Muslim Shrines of Harar plateu
Ethnic dynamic and changes -
By Ulrich Braukamper

The present inhabitants of the Harar plateau ascribe all archaeological sites and ruins of stone-built necropolis, store-pits, houses and mosques of that to the Harala. From the contemporary peoples of the area of our concern only the Harari were culturally close to the Harala as the representatives of a highly developed peasantry with centres.












Entrance to the walled city of Harrar. The Governor's gateway. Wells and self in foreground. (See page 117.)



**ቶጂያ**
**ነጃሺ ከዲር ሻሞ**
**ገጽ 212**
**ቁጥር 6**
**ኑረዲን አብድላ**

[በ19ኛውና በ20ኛው ክ/ዘ የሚነሱ ጸሐፊዎችና ተመራማሪዎች ሐርላም ሆነ ሱልጣኔቶች በተደፈነበት ዘመን ስለደረሱ የመላው የሓርላ አገርና የሱልጣኔቶች ታሪክ እንዲሁም የመላው የመሐል የደቡብ ምስራቅ የቀደምት ህዝቦች ታሪክ በሙሉ ከአደሬ ማህበረሰብ እና ከሐረር ከተማ ታሪክ ጋር እያምታቱ ጽፈዋል ። ቶጂያ ገጽ 212]

የኢትዮጵያ የሙስሊሞች ታሪክ ከሐረር እስልምና ስልጣኔ ጋር አዛምደው ካልጻፉት ከየትኛው ሃገር ጋር ነው አዛምደው የሚጽፉት? በምስራቅ አፍሪቃ ሐረርን የመሰለ ቀደምት ከተማ ከሐርላ ቅድመ ታሪክ እስከ ድህረ ታሪክ ከዋሻ ከሰቃ ሸሪፍ ፣ ለጋአዳ ፣ ሐርላ መንደር ፣ሰባቱ ጌይ ቱኹን ጌይ ፣ናርቲ ጌይ እስኻንቲጌይ ሩቂያጌይ ፣ሐረዌጌይ ሐሰንጌይ ፣ሳምቲጌይ ፣እድከ ሐረር አባዲር ጌይ መስጂዶች ፣ ቤቶች፣ የቁራን ትምህርትቤቶች ዱሪዎች ፣የቃዲ ፍርድ ቤቶች ፣ የዲዋን ቤቶች ፣ አሚር ቤቶች ፣ በቤት ላይ ቤት ግንቦች ፣ ረዘም ያለ በግንብ አጥር የታጠረ ፣ መድረሳዎች ፣ የራሷ ገንዘብ ሳንቲም አቅልጣ የቀረሰች ፣ መቃብሮች ፣ የአላህ ባሪያዎች የተቀበሩበት ፣ በርካታ ታላላቅ የነብዩ(ዐሰ)ቤተዘመዶች ሸሪፎች የተቀበሩበት ፣ በርካታ የታሪክ ማህደር የያዘች የአዷል ሱልጣኔት መቀመጫ በመሆና የታሪክ ማህዶሮቿ ሙዚየም አጣበው በነዋሪው ቤትም ሰነዶቿ ጢቅ ያለ ብቸኛ ከተማ ሐረር ናት ። እንደ ሐረር እድሜ የነበራቸው ከተሞች ሁሉ በጦርነትና በተፈጥሮ በተለያዩ ምክንያቶች ወደሙ ፣ ጠፉ ስልጣኔያቸው ቀጨጨ ፣ ዛሬ ላይ ጠፍተዋል ፣ ሐረር ግን በነበሯት ታላላቅ የአላአህ ባሪያ አሚሩል ሙሚኒን ተጠብቃ ህይያው ልትሆን ችላለች ምስጋና ለአለህ ይግባው አልሃምዱሊላህ ።
ወደ ዋናው ነጥቤ ስመለስ የቶጂያ ጸሃፊ የኢትዮጵያ ሙስሊም ታሪክ ከሐረር ጋር አምታተው ነው የጻፉት ብለህ የጻፍከው ፣ የራስህ መጻሃፍ ቢሆን አንተም ነጃሺ ከዲር እራስህ ቶጂያን መረጃና ማስረጃ የሰበሰብከው ከዚሁ ሐረር ድርሳናት የሐረሪ ጸሃፊዎች ፣ ከሐረር ሰነድ ፣ ከሐረር አሚሮች ስም ዝርዝር ፣ ከሐረር ሙዚየምና ሐረር ከተማ ላይ ከነበሩት የውጭ ሃገራት ዜጎችና መንገደኞች ወደ ሐረር እንጂ ወደ ሌላ ከተማ አልሄዱም ወደ ሐረር በመምጣት ነበር እነዚህ አውሮፖዊያን ቼሩሌም በለው በርተን ፊሊፕ ወይም ሮብቿ ሌላም ዋግነር በለው የፈለከው ተጋዥ ፣ የኢትዮጵያ እስልምና ታሪክ ጸሃፊዎች ትልቅ ግባት አድርጎ የሚጽፈው ሐረር መዲነቱል አውሊያ ታሪክ ፣ ቅርስ ፣ ሰነድ ፣ ጥንታዊዉ የእጅ ጹሁፍ ወይም የአካባቢው የትፊት መረጃ ነው እንደ ግባት ነው አንተም ከሌሎች ተሸለህ የራስህን ፈጠራ ታሪክ ብትጽፍም አብዛኛው ከሐረር ታሪክና ሰነድ ነው የገለብጥከው የታሪክ ተመራመሪዎችና መንገደኞች ወደ ሐረር መጥተው በታሪክና በቅርስ ውቅያኖስ ውስጥ እውቀታቸውን ያሰፉበት ዋናው ምክኒያት የሚከተለው ነው

1- ከቅድመ ታሪክ እስከ ድህረ ታሪክ ተከታታይ የሰነድ መረጃ ስላለ

2 - ቅርሶችና ሰነዶች በተገቢው ሳይወድሙና ሳይበላሹ ህያው ሆነው ስለተገኙ

3- የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ቅርስ ፣ ጥንታዊዉ ጹሁፎች ፣ ተሰብስብው ለምርምርና ለጥናት አመቺ ሆነው በሙዚየም በተገቢው ቦታ ስለሚኙ

4- ከአንድሺ አመታት በላይ ያስቆጠሩ ግንብ ቤቶች ፣
መቃብሮች ፣ ዱሪዎች ፣ በርካታ መቃብሮች ፣ ቅዱሳን ቦታዎች ፣ ታላላቅ ኡለማዎች መቃብራት ስለሚገኙበት

5- እስልምና ከሐረር ወደ ተቀረው ምስራቅ አፍሪካ በሰላምና በፍጥነት ስለተሰራጨ

6- የኢትዮጵያን ሙስሊም ስልጣኔ በበቂ ሁኔታ ስለተሰነደ

6- ይህ ድንቅ የምስራቅ አፊሪካ የእስልምና ስልጣኔ በመጨረሻም በ UNESCO በ2006 እኤአ በዓለም ቅርስነት በመመዝገቡ ።

ከላይ የተዘረዘሩት ሃቅ ሆኖ ሳለ ለቶጂያ ደራሲ ይህ ሊዋጥለት አልቻለም ነጃሺ ሻሞ በመርፌ ቀዳዳ ታክል ሚጢጢ የታሪክ እውቀት እንደ ውቅያኖስ የገዘፈ የሐረር ትክክለኛ ሙስሊም ታሪክ ያልተሰሙ የቶጂያ ታሪክ በማለት በፈጠራ

ትርክት መበረዝ አትችልም ስለሐረር ታሪክ በቂ እውቀት ምርምርና ጥናት ያደረክም አትመስለኝም ። ያገር ውስጥም የውጭም ተመራማሪ ሐረር መጥቶ መረጃ ሰብስቦ በታሪኳ ያልኮሯ ያልተገረመ ፣ ያልተመሰጠ የለም ። ወራቤ ፣ አዲስ አበባ ተቀምተህ ስለ ሐረር ታሪክ እጽፈለሁኝ ካልክ ብናኝ የምታክል ትንሽ እውቀት ለኪሳሯ ይድርጋል ዛሬ ይህ ነው የገጠመህ ።

መረጃ
የአገር ውስጥና የውጭ ምሁራን ሙስሊም ክርስቲያን
ስለ ሐረር የጻፉት ስለ ሐረር ታሪካዊ ፣ እስላማዊ ፣ ጥንታዊነት መሆኑና ከኢትዮጵያ ሙስሊሞች ታሪክ ተያያዥነታቸው የመሰከሩ ጥቂት ለሙና በመረጃ አቀርባለሁኝ ቶጲያ በገጽ 212 ያቀረበው ስህተት
መረጃ ለማመልከት ነው
ፍርዱን ለአንባቢ ትቻለሁኝ

Avishai Ben-Dror ,
Emirate, Egyptian, Ethiopian
P 15
Harar is one of the oldest Muslim city of East Africa . The city located about 325 miles east of Addis Ababa . It is Often Called Madinat al Awliya "the city of Holies" and that is how it is perceived by its resident, many of whom regard themselves as the descendants of the city's holy founder. There are 356 holy sites within Harar's Walls , mainly tombs of emir, religious preacher, and descendants of clerics .

ሼኽ መሐመድ ኢብራሂም
የሐበሻ ከዋክብት
ገጽ 52
በሐረር እስልምና እንዴት ተሰራጨ ?
ቁራንስ እንዴት መማር መስተማር ተጀመረ?
ቁራን ጌይ የሚባለውን የቁርዓን መማሪያ ማዕከል ለመጀመሪያ ያቋቋሙት ሼኽ አባዲር ናቸው የመአከሉ የመጀመሪያው አስተማሪም ሰው ሱፊ ያህያ መሆናቸው ይወሳል ።
እስልምናን ለማሰራጨት ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል ለልዩ ልዩ ማህበረሰቦች ቋሚ መምህራን ፣ ቃዲ ( ዳኞች ) መመደባቸው ነው ። ከነዚህ ኡለማ መካከል አንዳንዶቹ ተልካቸውን አሳክተው በኖሩባቸው ክልሎች ተቀብረዋል ። አንዳንዶቹ ችግሮችን ለማለፍ በለመቻላቸው ወደ ሐረር ተመልሰዋል ።

Avishai Ben-Dror
P 155
ሐረር ምን ያህል ጠንካራ የእስልምና ሐገር እንደነበረችና እስልምና ያልሆነ መግባት ያልቻሉ አውሮፖኖች የጻፉት ሰነድ የሚከተለው ነው
In early April 1881, Father Cahagne and his men set out from Zeila to Harar . As they prepared to enter the City , afellow missionary in Cahagne's party Wrote : " Harar spreads out on ahigh plateau, and over a lovely valley .... agricultural terraces are built in the Valley . It all looks like a garden . Above all these stand two or three minarets , and two or three large buildings that the Egyptians recently built . A wall surrounds it and is meant to defend them . We stand before the mysterious Capital, Which Europeans have not entered for hundreds of years ."

[The Conquest of Abyssinia]
page 13
The town of Harrar, which is here expressly referred to as part of the land of Sadaddin, had replaced Dakar as the Adal Capital only in 1520.on the history.

ሴረ የስልጤ ህዝብ ታሪክ ፣
በከይረዲን ተዘራ ፣
ገጽ 26
ስለ ሐረሪ ሐርላ ማህበረሰብና ከአባዲር በፊት በመሬቱ ነባር መሆኑ አያሌ ጎሳዎችና ማህበረሰቦች የተከፈለ በእንስሳት እርባታ በእርሻና በንግድ ተግባራት የተሰማራ ብሎም በመንግስታዊ ስርዓት የሚኖር አንድ ሐርላ የተባለ አገርና ህዝብ እንደነበረር ከዘመኑ መረጃዎች በትክክል ለማወቅ ይቻላል ።
ሴረ የስልጤ ህዝብ ታሪክ
ገጽ 140
የተገኙት ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት የመጀመርያዎቹ የሀረር አንባ ነዋሪዎች ሀርላ የሚባሉ ናቸው ። እነዚህም ስዎች ከ14 ኛው እስከ 16ተኛው ክፍለ ዘመን በጣም ያደጉ የግድብ ስራ ስልጣኔና የድንጋይ ግንብ ስራ ችሎታ የነበራቸው ነበሩ ።

ባሕሩ ዘውዴ
የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ : 2007
ገጽ 19
በስተ ምስራቅ የሚገኘውና በአሚር የሚተዳደረው የሐረር መንግስት ደግሞ በፊናው አንድ ትልቅ የእስልምና ሥልጣኔና እምነት ማዕከል ነበር ።

Avishai Ben-dror
P 71
እስልምና ትምህርት አስተምሮ ሐረር ምን ደረጃ ላይ እንደነበር የሚከተለውን ነጃሺ ከዲር  ከስልጤ ቀደምት አያቶችህ እያልክ ከጻፍከው ሃገር  ጋር አንጻጸረው
Referring to Harar's Muslim inhabitants, Muhtar and Fauzi wrote
The behavior of the people of Harar is praiseworthy. In terms of intelligence, they are motivated by pursuit of profit snd love of the homeland . They are disposed toward learning. All the Children read in the katatib ( plural of kuttab, elementary Quranic schools ) throughout the day . The older people continue to read at night as well. The others work at learning the sharia with the experienced  among the ulama. This is for the purpose of becoming expert in Islamic law . Their greatest love is for the madhhab (school of thought) al- Shafii. The older ones in the city receive Islamic education according to al-Shafii school of thought . Islam is seen as the tie that binds, in addition to the colonial attachment. The al-Shafii adherents in Egypt are proud of the people of Harar, who are developed to their school of thought, especially in light of the fact that they live in the heart of Africa.

አብዱላሂ ሼኽ አህመድ ቡህ

1998 ዓል
ገጽ 1
የሐረሪና የሐረር ከተማ ታሪክ
ሐረር በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ከተሞች ሁሉ በሙስሊሙ ዓለም ዘንድ ታዋቂነት ክብርና ዝና ያላት ከተማ መሆንዋ ይታወቃል ከተማዋን ለዚህ ያበቃት በምስራቅ አፍሪካ የእስልምና ሃይማኖት ማዕከል በመሆንዋ ነው ( ዋልተር ፍዝጊራለድ የአፍሪካ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ና ጅግራፊ ገጽ 464/1984)
( Africa : Asocial, Economic and political Geography of its Major Regions . Walter Fitzgerald )
ገጽ 1-2
ሐረር ከተማ ራሷን የቻለች እስላማዊ አስተዳደር የነበሯት ከተማ ከመሆናም በላይ ለእስልምና ሃይማኖት ባህል እንዲሁም ለንግድ መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጾ ያደረገች ከተማ ናት ። በሐረር ከተማ የእስልምና ሐይማኖት ለማስፋፋት የመጡ ብዛት ያላቸው አልአሽረፍወሹሃዳ ( የነቢዩ መሐመድ ሰዐወ) ዝርያቸው ተቀብረዋል ።

Avishai Ben-Dror
Emirate,Egyptian,Ethiopian
pp 17
የሐረር ሳንቲሞች ዘገባ
ስለ ሐረር ጥንታዊው ገንዘብና ሳንቲሞች በተመለከተ የሐረር ጥንታዊው ገንዘብ ሣንቲም አጀማመር መቼ ሐረር ላይ ተጀመረ ? ለሚለው ጥያቄ አብዛኛው የውጭ ሃገር ተመራማሪዎችም ሆነ በሃገር ውስጥም የሐረር ጥንታዊው ገንዘብ ሳንቲሞች የተጀመረው በ16ኛው ክ/ዘመን አሚር ኑር ቢን ሙጃሂድ ዘመን መሆኑን ሁሉም ተመራማሪዎች የተስማሙበት ነው :: ይህንን በተመለከተ አቪሻይ ቢንዶሮር የሚከተለውን ያስነበናል

"(Amir) Nur was the first ruler of Harar who coined local currency, the main one being the mahlak. [Emirate,Egyptian,Ethiopian  Avishai Ben-Dror pp 17]"

ተክለጻድቅ ሙኩሪያ
የግራኝ አህመድ ወረራ
ገጽ 46

ስለሐረር ጥንታዊው ሳንቲሞች የኢንሪኮ ቺሩሊ ዘገባን ዋቢ በማድረግ የሚከተለውን ያስነብባል“ የወላስሞች መደብ ከ1512 ዓል ወዲህ ከአዳል (ደከር) ወደ ሐረር በዞረበት ብዙ ዓረቦች ከማዶ ከዓረብ አገር እየመጡ ከአዳሎችና ከሱማሌዎች ጋር በኖሩበት ሰዓት የሐረር ህዝብ የመገበያያ ገንዘብ እንደነበራቸው ለማስረዳት አቡበከር ኢብን መሐመድ ሻም በአልዊ የሚባለው ዓፄ ገላውዴዎስ በሞቱበት ዓመት በሐረርጌ በተነሳው የረሃብ ጽናት የእህሉን ውድነት ከተረከበት ላይ አንድ መለኪያ (ቁና ) በቆሎ 12 አሽራፍ አንድ መለኪያ አሞሌ ጨው 25 አሽራፍ የበሬ ዋጋ 300 አሽራፍ ከዚህም በላይ ሆነ ሲል ጠቅሷል” እንደገናም መረጃውን በቀጠል ተክለጻድቅ ሙኩሪያ
“የሐረርጌ ሱልጣኖች ወይንም የነ አሚር ኑር ግዛት የመገበያያ ገንዘብ ሊኖረው የቻለው ይኸው ሐረርጌ በዘይላ ወደብ አማካይነት በቀይ ባህር ማዶ ከአሉት ከዘቢድ አረቦችና ቱርኮች ጋር የሥልጣኔ ግንኙነት አድርጎ ሸቀጥ ለሸቀጥ እየተለዋወጠ ንግዱን በማስፋፋቱ ምክንያት ይሆናል”

አል መነህል ( የአፋር ታሪክ )
ሼኽ አቡ ሸዋሪብ አልሐረሪ
ገጽ 644-645

ሼኽ አቡ ሸዋሪብ አልሐረሪ ይባላሉ 1100 ዓመተ ሂጅሪያ / 1688-89 እኤአ የኖሩ ምሁር ናቸው

በአፋር የአሽራፍ ጎሳ የሆኑት ሼኽ አቡ ሸዋሪብ አልሐረሪ የእኚህ ታላቅ የሃይማኖት ምሁር አባት የዘር ሐረግ ከሰይድና አሊ ይመነጫል :: በአውሳና በታጁራ የሸዋሪብ አል ሐረሪ ዝርያወች በብዛት ይገኛሉ :: በአፋሮች Legend ትርክት ሼክ አቡ ሸዋሪብ አል ሐረሪ ቅድመ አያቶች በአፋር ይኖሩ እንደነበሩና ከዚያም ወደ ሐረር በመሄድ እዚያም በአዳል ሱልጣኔት የመለሳይ ቡድን መስርተው ጥሩ አስተዎጾ ያበረከቱ ሲሆን ከነዚህም ልጆች አቡ ሸዋሪብ አልሐረሪ ወደ አፋር ተመልሰው አፋሮችን በእስልምና አንጸዋል

በአፋረኛ ኦሊቶ ማለት የዙፋኑ ባለቤት ተብለዉ የሚጠሩት ከየመን ሳዳት ጌቶች አንዱ ናችው :: አፋሮች የአቡ ሸዋሪብ ቅድመ አያቶች በአፋር ግዛት ከታጁራ በስተደቡብ ምዕራብ ከምትገኘው ከጎባድ ክልል ይኖሩ እንደነበረና ከዚያም ተነስተው ወደ ሐረር እንደወረዱ ሲያስረዱ ሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች ደግሞ አቡ ሸዋሪብ አል ሐረሪ ቤተሰብ ከሐረር ወደ አፋር የመጡና የሐረሪ ብሄረሰብ የሆኑ እዚህ አፋር መጥተው ህዝብን ወደ እስልምና የመለሱና ያስተማሩ እስልምናን በአፋር እንዲጠናከር ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ እንዲሁም በርካታ የእስልምና መጽሐፍቶችን የጻፉ ታላቅ ዓሊም ( ሊቅ) ናቸው ::

ሼኽ አቡሸዋሪብ የሞቱትና የተቀበሩት በታጁራ ከተማ ሞተው እዛው ተቀበሩ :: [አል መንነህል ገጽ 644-645]

ሼኽ አቢ ዘሪ አልሐረሪ
አልመነህል
ገጽ : 223-224
ከሐድራሞት የመን ወደ ዘይላ : አፋርና : ሐረር በ15 ክፍለ ዘመን የመጡ የእስልምና ምሁር ናቸው ::

በአፋር እስላማዊ ትምህርትና ስልጣኔ አሻራ ካሳረፉ የሙስሊም ምሁራን አንዱ ሼኽ አቢ ዘሪ አልሐረሪ ናቸው :: የሼኹ ትክክለኛ ስማቸው አል ሰይድ ሼኽ ኢብራሂም ቢን አደም ቢን አህመድ ቢን ሼኽ አቢ ዘሪ ቢን ኡመር አል አለዊ አል ሐረሪ ይባላል :: በ15 ክፍለ ዘመን እስልምናን በሐረርና በአፋር አካባቢዎች በማሰራጨትና በማስፋፋት ትልቅ ድርሻ በማበርከታቸው ጉብዝናቸውን ለመግለጽ “ወናጋች”(አንበሶች) በማለት ይጠሯቸው ነበር

አል ቁጥብ ከቢር አል ሼኽ ኡስማን ቢን አህመድ አለዊ አልሐረሪ የአቢ ዘሪ ዝርያ ናቸው ናቸው :: በሂጂሪያ 1304 በቤይሉል ሞተው ተቀበሩ የመቃብር ሥፍራውን የሰራው ጣሊያናዊው ገዢ ሲሆን ይህም የሆነው በህልም ስላያቸው ነው
በ1430 እኤአ ሼኽ ኢብራሂም አቢ ዘሪ አል ሐረሪ በሐረር ከተማ በአስማ ዲን በሪ በሚባለው አካብቢ ባብ አንሳር የሚባል አዋች (Shrine) ዶሪ እንደ ትምህርት መዕከል ለእስልምና ማስተማር ተጠቅመውበታል ::
በአፋር የእስልምና ኃይማኖት በሰፊው አሰራጩ በዚህም አቡና በሚል ቅጽል ስም ታላቅ ማዕረግ ስም ተሰጣቸው :: መጨረሻም ሼኽ ኢብራሂም ወደ ዘይላ በመሄድ እስልምናን ሲያስተምሩ እዛው ዜይላ ላይ ሞተው ዘይላ ተቀበሩብ በየመን ሐድራሞት ከሚገኘው አርባ አራት ገልማ ወይንም ዶሪ አንዱ የሼኽ ኢብራሒም አቢ ዘሪ አንዱ ነው ::
[አልመነህል ገጽ : 223-224]

አልመነህል( የአፋር ህዝብ ታሪክ )
ገጽ 567-568
የአቢ ዘር አል ሐረሪ
የአቡና ተወላጅ ከሆኑት በአፋሮች ዘንድ ከፍተኛ ክብር ይሰጣቸዋል ፣ ቅዱስ ቁርዓንን በቃላቸው ያጠኑ ብዙ ሰዎች በአፋር ግዛት ይገኛሉ ፣ የአቡና ተወላጅ ከሆኑት ሰዎች መካከል ቁርዓንን ማንበብ የማይችል ሰው አይገኝም ፣ የአቡና ተወላጅ በመባል የሚታወቁት የአቢ ዘር አልሐረሪ ተወላጆች ናቸው ። አቢ ዘር አል ሐረሪ እጅግ በጣም የታወቁና

በሐረር ከተማ ሞተው እዛው የተቀበሩ ናቸው ። የአቡና ተወላጅ የቁርዓን መምህራን አፋር ዘንድ ከፍ ያለ ግምት ይሰጣቸዋል ። በለቅሶና በሰርግ ቤቶች የተለየ ሥፍራ አላቸው ። ከሚታረዱ ከብቶች ሥጋ እና ቆዳ የተለየ ድርሻ ይመደብላቸዋል ። በአለባበሳቸውም ቢሆን ከአብዛኛው ህዝብ ይለያሉ ። [ጣቂያ] በመባል የሚታወቅ ቆብ ያጠልቃሉ ፣ ነጭ ጥምጥም ጠምጥመው ነጭ ቀሚስ ያጠልቃሉ ። በአንድ እጃቸው ምርኩዝ በሌላ እጃቸው ረዘም ያለ መቁጠሪያ ጨሌ ይይዛሉ ። ስለ እነዚህ የቁርዓን ትምህርት መምህራን ስም ሲነሳ የሼኽ አህመድ ናሊዩ እና የሼኽ አልሐጅ መሐመድ ሳሊህ አል አህመዲ ስም ሳይጠቀስ አያልፍም ።
በሼኽ አቢ ዛሪ አልሐረሪ ስም የሚጠሩ ሶስት ዛዊያዎች ይገኛሉ እነዚህም ዛዊያዎች
1- በ ደለሚ ደሴት
2- በ ምዕድር በዕዊሲይና
3- በፈሪይዳሎ አካባቢ ይገኛሉ

አል መነህል (የአፋር ህዝብ ታሪክ )
ገጽ 313
ሐረር እና እስልምና
ሐረር በወቅቱ ከሌሎች ከአካባቢዋ ከነቡሩ ግዛቶች በሙሉ የተሻለ የሃይማኖታዊ ተቋማት እንደነበራት ፣ ከሌሎቹ በተሻለ ሁኔታ የሸሪዓን ፣ የቁርዓን እና የፊቅሂን ትምህርት በማስተማር ረገድ ከፍተኛ አስተዎጾ ታበረክት እንደነበረች ነው ። ሐረር ከማዕከላዊ መንግስት በመገንጠላ በሐረር በኩል (ወደ አፋር) ይመጡ የነበሩ የሃይማኖት እና የቁርዓን አስተማሪዎች መምጣት በማቆማቸው አፋር በተከታዮቻ ዘንድ የነበራት አቅም እየተዳከመ ሄደ ።

ተክለጻዲቅ ሞክሪያ
አጼ ዩሐንስ
ገጽ 285
ስለ ሐረርና እስልምና የሚከተለውን ያስነብባል
በ1512 ዓል አካባቢ ከደከር ወደ ሐረር ተዛውረው ደንበኛ መቀመጫ አደረጉ ። በዚሁ ጊዜ ከቀይ ባህር ማዶ ያሉት አረቦች እየበረቱ በሔዱ መጠን ወደ አውሳና ወደ ሐረር እይሰረጉ በመግባት የሐረርጌ የአካባቢው እስላሞች ተወላጅ አጠናከሩ ። በዚህ ጎን የሃይማኖት መሪዎች (ሼኾች)ያልተማረውንና ያላመነውን በጋብቻም በንግድም እየጠገኑ እያስተማሩ ወደ እስልምና በማግባት በቀን ብዛት የእስላሙ ቁጥር አበራከቱት ።

ዓይን አብራዎች
ተሾመ ብርሃኑ ከማል
ገጽ 141
ሐረር ከ12ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ በሃይማኖት አባቶችና የኢስላም እውቀት ባላቸው እንዲሁም የኢስላም እምነት በሚያስከብሩ ሱልጣናት ትመራ እንደነበር ይታወቃል ። በሐረር ( የዱሮውን ሐረርጌ ይጨምራል) ውስጥ እጅግ የታወቁ የሃይማኖት አባቶች እንዳሉ የታወቀ ቢሆንም ታሪካቸው ግን በሚገባ አልተመዘገበም ።

አህመዲን ጀበል
3ቱ ዓጼዎች እና ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች
ትግልና መስዎዋትነት 2008 ዓል
ገጽ 76
ሐረር
በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሐረር እንደ አክሱም የምትታይ ጥንታዊ ከተማ ነበረች ። እኤአ 969 በአሚር ሐቦባ ከተመሰረተችበት ጊዜ አንስቶ ከሺህ ዓመታት በላይ ኢስላማዊ ከተማ ሆና ዘልቃለች ። በርካታ ያልተነገረ ታሪክ ያላት የኡለሞች ፣ የሙጃሂዶች ፣ እና የበርካታ ቅርሶች ባለቤት ከተማ ነች ።

ሐረር ሙስሊም ያልሆነ ሰው ፈጽሞ የማይረግጣትም ነበርች ። በዩኒስኮ ( UNESCO ) በዓለም ቅርስነት ተመዝግባለች ። ሙስሊም ነጋዴዎች ከተለያዩ ዓለማችን ክፍል በመምጣት ለንግድ የሚገናኙባት ማዕከል ነበረች ። የአዳል ሱልጣኔት ዋና ከተማ ከሆነችበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ብሎም የኢስላም መገለጫ ነበረች ። በርካታ ኡለማዎች ለደዕዋ ወደ ሐረር ጎርፈዋል ። ከነዚህ መካከል ሼኽ ዑመር ሪዳ ( በሐረሪዎች አጠራር ሼኽ አባዲር ይገኙበታል ። )

አህመዲን ጀበል
የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከ615 -1700
ገጽ 106
እስላም ከዛጉዌ ሥርዎ መንግስት ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ እምብርት ድረስ የዘለቀ መንግስት በሸዋ አቋቁሞ ነበር ይታወሳል ... በዛጉዌ ዘመንም በሌሎች አካባቢዎች በስፋት በመስፋፋት ከሸዋ ሱልጣኔት ውጭ በሐረር ፣ አዋሽ በሌሎች አካባቢ ከ11ኛው ክ/ዘመን በፊት ሊስፋፋ ችላል ። በሐረር አካባቢ ባቴ ሐይቅ አሥራ ስምንት የሙስሊም መቃብሮች ተገኝተዋል

አፈንዲ ሙቱቂ
አዳል 1ኛ መጽሃፍ
ገጽ 6
እስልምና በኢትዮጵያ የረጅም ዘመናት ታሪክ አለው ። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንደ ሌላው ህዝብ ሁሉ በሀገራቸው ላይ አስደማሚ ስልጣኔ ሲገነቡ ኖረዋል ። ይሁን እንጂ ከጥንታዊ አሻራቻቸው መካከል የሚበዙት የዘመን ተግዳሮቶችን መሻገር አልቻሉም ። በተለይም በመካከለኛው ዘመን በተመሰረቱት የሙስሊም መስተዳድሮች በህዝባቻቸው የተሰሩ ልዩ ልዩ የህይወትና የታሪክ መዘክሮች በተፈጽሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች የመጽፋት ዕጣ ገጥሞአቸዋል ። አንዲት ከተማ ግን ከመአቱ ተጠብቃ ቁሳዊና እና ሰብዓዊ ቅርሶቿን እንደያዘች እስከ ዘመናችን ድረስ ዘልቃለች ። ሐረር

አፈንዲ ሙተቂ
አዳል 1ኛ መጽሐፍ
ገጽ 6
ሐረር ከ1415-1577 ዓል በነበረው ዘመን በኢትዮጵያ እና በመላው የአፍሪቃ ቀንድ ህዝቦች ታሪክ ላይ መጠነሰፊ አሻራ ትቶ ያለፈ የአዳል ሱልጣኔት አካል ነበረች ። በተለይ ደግሞ ከ1520- 1577 ዓል የሱልጣኔቱ መዲና በመሆን አገልግላለች ።
የሐበሾችና የዘይላዕ ሙስሊሞች የመካከለኛ
ዘመን መንግስታት ፖለቲካ ግንኙነት ታሪክ
(ኢለቀት ሲያሲያ በይነ ሙስሊም ዘይለዕ ወነሳራ ሐበሻ)
ዶ/ር ረጀብ መሐመድ ዓብዱልሐሊም
ካይሮ ዩኒቨርስቲ 1985
ገጽ 63
የሃበሻ ክርስቲያኖችና የዘይላሙስሊም መንግስታት ግጭት አስመልክቶ የሃበሻ ክርስቲያን የሙስሊሞችን የንግድ መተላለፊያ መስመሮችን ለመቆጣጠር ተነሱ ። ስለሆነም በተለይም " የሐረር ኢስላማዊት ከተማ" ዘይላዕ ፣በርበራና ታጁራን ከሐበሻ የንግድ ቃፊላ( ሲራራ) የሚያይዝ ሚና ስላላት ልዩ የትኩረት ዓይን ጣሉባት ።

በኢትዮጵያ የማክዙማይትና የሃሽማይት ወላስማ ስርወ መንግስት ስልጣኔና ታሪክ
የአርጎባ ህዝብ መነሻ
አህመድ መሐመድ ኢብራሂም

ገጽ 18
በኢትዮጵያ የሙስሊም መንግስታት ሥልጣኔና ታሪክ ተከታታይ የሆኑት ሂደቶች ማለትም ከ896 -1285 ማከዙማዊት የሸዋ ሱልጣኔት ከ1285 -1415 የሃሺማዊት የይፋት ወላስማ ሱልጣኔት ከ1415 - 1577/የሃሽማይት ወላስማ አደል ሱልጣኔት ከ1527 - 1543 በሐረርና ደንቢያ ማዕከላዊ የኢማሙ አህመድ ግራኝ የሃሽማይት ወላስማ አደል ሱልጣኔት እና ከ1544 - 1567 የአዳሉ አሚር ኑር የሐረር የጆጎል ግንብ ከአርጎባ ህዝብ ታሪካዊ መነሻና ማንነት ጋር ተያይዞ አዲስ የበቀሉ አሰራሮች እንደዚሁም ክስተት ዕድገቱን የተከተለ የመንግስት ምስረታ ሂደትና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ነው ።

በኢትዮጵያ የመኽዙማይት
የአርጎባ ህዝብ መነሻ
ገጽ 31-32

የሸዋ ሱልጣኔት ከ896 እስከ 1285 ድረስ ለ400 አመት ከዚያም ለቀጣዩና ወራሹ የይፋት ወላስማ ሱልጣኔት በ1285 ጀምሮ የፖለቲካ ማዕከሉ ወደ ሐረር እስከ ተዛወረበት ጊዜ ድረስ ለ 5 ምዕተ ዓመት የሁለቱ ተከታታይ ሱልጣኔቶች ማዕከላዊ መቀመጫቸው ሆኖ ያገለገለ ታሪካዊ ስፍራ ነው ። ይህ ጥንታዊና ታሪካዊ ስፍራ በደቡብ አፋር አርጎባ ልዩ ወረዳ እንደሚገኝ ከ13 የገጠር ቀበሌዎች አንዱ እንደሆነና ገበሮች እንደሚባል ታውቋል ።

የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓት ጅምር ካፒታሊዝም
ዶ/ር ላጲሶ ጌ . ድሌቦ
ገጽ 70
ሐረር በጣሊያን ወረራ
በፋሽስት ኢጣሊያ የሰፈራ መንግስት በ1929 አዲስ ባዋቀረው አስተደዳራዊ ግዛት ሐረርጌ- አርሲ ክልል በማወሀድ ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች እድል ሰጠ በዚህ መሰረት በሐረር ብቻ
47 ቃዲዎች (የመደበኛ ፍርድቤት ቃዲ ዳኞች ተሾሙ)
40 የዲዋን ሃላፊዎች ( የሃይማኖት ሹም ተሾሙ )
100,000 ሊራ ደሞዝ በጀት መደበላቸው
በሐረር የቁራን ትምህርት ቤት 450 ተማሪዎች ነበሩት
ለአፍሪካ ቀንድና ለቀይ ባህር አካባቢ እስላሞች በሐረር ከተማ የእስላማዊ ጥናት ዩኒቨርሲቲው ለማቋቋም ፕላን ነበራቸው ።
በ1931 ብቻ 3585 የመጀመርያው በአየር ወደ ሐጅ ለማድረግ በይፋ ወደ ሰውዲ አረቢያ ጉዞ ተደረገ

ፕ/ር አደም ካሚል
የኢትዮጵያ ሙስሊም ታሪክ ተመራማሪ
በሚዲያ

ሼኽ ፈቂ ሐሺም ሐረር ትምህርት ማዕከል ከፈቱ
(1123-1189 ሂጅሪያ
ሼኽ አህመድን ከሰሜን ወሎ ተጠባባቂ አደረጉ
ፈቂ ዙቤይርን የንጉሱ ሼኽ ( ሼኽ መሐመድ ሻፊን) ተጠባባቂ አደረጉ ፣ ---> ሼኽ ፈቂ ሰይድ ዙቤርን ተጠባባቂ አደረጉ ---->ሼኽ ጀማለዲን አኒዬ ( የዳናው ሼኽ ) ተጠባባቂ አደረጉ --->ዳኒየል አወል ( ሼኽ አህመድ አደም ) ተጠባባቂ አደረጉ --->ዳኒየል ታኒ ( ሼኽ መሐመድ ያሲን ----> ሼኽ አብዱል ኑር አብደልከሪም ( ከዳና ውጪ )

ተጠባባቂ አደረጉ) ---> ሼኽ መሐመድ ዘይን ወደ ዳናው አሊሞች መለሱት ---> በ1967 በተፈጠረው ችግር ተቋረጠ  በማለት የጥንት የእስልምና አስተምሮ ከሐረር ወደ ተቀረው እንደተሰራጨ
በተደጋጋሚ በሚዲያ በመቅረብ የጥንትኡለማ  የአባቶች አስተምሮ ሰንሰለት አስረድተዋል ።

ጥሮነ
አብዱልፈታህ አብደላ
ገጽ 180
ሐረር የቃድሪያ እስልምና ጠሪቃ መስራች ከተማ በኢትዮጵያ
በመጀመርያው ጊዜ የቃድሪያን ጠሪቃ በኢትዮጵያ ያስተዋወቁት ሰይድ ሼኽ ሐሺም አል ሐረሪ ሲሆኑ ከርሳቸው የተቀበሉት ሼኽ አህመድ ሳልህ ናቸው ። ቀጥሎም ሼኽ ፈቂህ አዙበርይ ጋጉሪ ሼኽ መሐመድ ሻፊ አንጉሲ እያለ በርካታ ሼኾች በቅብብሎሽ ስም ተዘርዝረዋል









የሐረሪ ጥንታዊዉ የኸሊሊ ጥበብ